# ዘፋኝ አሰኛቸው?

(ከአየነው ምስክር ዘጎፋ)

ማሕሌተ ያሬድ፣አልግባህ ቢላቸው፣
ያሜሪካ አመል፣ተቀስቅሶባቸው፣
አባ እንደ ጎረምሳ፣ ቢፋኝ አማራቸው።

ያባቶች ሃይማኖት፣ አወይ ተዋሕዶ!
አለቀ ታሪክሽ፣ ተንዶ! ተንዶ!
እግዜአብሄር ጥሎብሽ፣ አባት አጋሚዶ።

ወጣቱ ጳውሎስ፣ ከዓም ሲመንኑ፣
ሁሉንም በመናቅሌ፣ አስኬማ ሲጭኑ፣
ጽሎታቸው ሰምሮ፣ ባለገርል ሆኑ።

ታጋዩ ጳውሎስ፣ አባ ነጭ ለባሹ፣
ዘፋኟን ፈወሷት፣ በመስቀል እያሹ፣
ምእመናን ጥግ ያዙ፣ እንዳትበላሹ።
በገርሉ ትሩፋት፣ የታወቀው አባት፣
ለምን ይወገዛል፣ በገሀድ ቢሳሳት!?
እስከ መቃብር ነው፣ አመልና ጅራት።





ያሜሪካ ቅሬ፣ የዶሮ አይን የበላች፣
በምኗም በምኗም፣ እየጠቃቀሰች፣
ባለገርሉን አባት፣ ፈተና ላይ ጣለች።
የያዛት አባዜ፣ እያስወገሻት፣
በመስቀሉ ጥላ፣ አባባሱባት።

«ወደ ቅሬ ያየ፣ የተመለከታት፣
በልቡም ጎምጅቶ፣ ሳስቶ የተመኛት፣
ፈጽሞ በልቡ፣ አመነዘረባት።»
ጳውሎስ ያለውን፣ ጳውሎስ ከሻረ፣
የማን ወኪል ሆኖ፣ እስከዛሬ ኖረ?!
የሚሰማ ጠፋ፣ ሁሉም ደነቆረ።

አያሌው ታምሩ፣ ሊቀ ሊቃውንቱ፣
ትናንትና አይደለም፣ ዛሬ ነው የሞቱ፣
ከዚች ቅሬ አርሆ፣ ከአይነ ሌባይቱ፣
ጉዳቼውን በሰሙ፣ አባ ሲጫወቱ።

ሲኖዶስ በሃሜት፣ እንደተወጠረ፣
መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ ማተቡን አሰረ፣
ከነጓደኞቹ፣ ማተቡን ያልጣለ፣
ከአባቶቹ ይልቅ፣ ዳንኤል ተሻለ።

እናንተ ምሁራን፣ ብርታቱን ይስጣችሁ፣
ረሀብ፣ እስራት ሌላም ቢገጥማችሁ፣
ከክርስቶስ ፍቅር፣ ማንም አይለያችሁ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com